
# <u>የእንስሳት አብዮት</u>

ትርጉም፤- በመስፍን ማሞ
ዕይታ፤- በአብይ አፈወርቅ




ከሁሉ አስቀድሞ ይህንን በከተማችን የመጀመሪያ የሆነውን የመፅሀፍ ምረቃ ስነ ስርአት ላስተባበሩት ልባዊ የሆነ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ። ከሁሉም በላይ ግን በሲድኒ የመጀመሪያችን በሆነው የመፅሀፍ ምረቃ ዝግጅት ላይ ለመገኘት የእረፍት ቀናችሁን ሰውታችሁ ከሩቅና ከቅርብ ተጉዛችሁ ለመጣችሁ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ የከበረ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ። ይህ አይነቱ መሰባበሰብም ቀጣይ እንጂ የመጨረሻችን እንደማይሆን ሙሉ እምነት አለኝ። ይህንን ካልኩ በኋላ በቀጥታ ወደ ተሰጠኝ የእለቱ ፕሮግራም - የእንስሳት አብዮት ቅኝት - አመራለሁ።

በብእራቸው ውበትና ጥንካሬ የማደንቃቸው በርካታ ደራሲያን አሉ። በተለይ ግን ሁለት አይነት ደራሲያን ሁሌም ያስገርሙኛል። አንድም - ስለመጪው ዘመን ይፅፉና ትንቢታቸው በዘመናት ሂደት እውን ሆኖ ይገኛል። አልያም ደግሞ በአንድ ውሱን ስፍራ ከተተገበረ ታሪክ ተነስተው ሁነቱ የጊዜን ደመና ጥሶ፤ የቦታን ኬላ ሰብሮ - የሁሉን እውነት ማሳየት እንዲችል አድርገው ያቀርቡታል። በመጀመሪያው ረድፍ ያሉትን እንደ ነቢይ ልናያቸው እንገደድ ይሆናል። ሁለተኞቹን ግን ሰፊ ምናብ የታደሉ ሊቅ ደራሲያን ልንላቸው እንችላለን።

አብነት ልጥቀስ፦

ሞርጋን ሮበርትሰን የተባለው ደራሲ እኤአ በ1898 ዓ/ም “Futility” (ከንቱነት) የተሰኘ መፅሀፍ ፃፈ። በጊዜው እምብዛም አንባቢ አላተረፈም ነበር። ይሁንና ከአስራ አራት አመታት በኋላ በ”ከንቱነት” የተተረከው ታሪክ በሚያስደንቅ መልኩ እውን ሆኖ አለምን ጉድ አሰኘ። ያቺ በአነስተኛ ኮፒ የተሰራጨች መፅሀፍም እንደ አዲስ በሚሊዮናት ቅጂ እየታተመች ከአለም ዳር እስከ ዳር ተነበበች።

ሞርጋን ሮበርትሰን የፃፈው “ታይታን” የተባለች፤ በዘመኑ ከሁሉ የላቀች ትልቅና ፈፅሞ የማትሰምጥ ስለመኗ የተመሰከረላት መርከብ በአትላንቲክ ውቅያኖስ ላይ ስለገጠማት የመስጠም አደጋ ነበር። ከ14 አመታት በኋላ እኤአ በ1912 ዓ/ም ደግሞ በእውኑ አለም “ታይታኒክ” የምትባል ከታይታን ጋር ፍፁም አንድ የሆነ ዝና ያተረፈች መርከብ በተመሳሳይ ቦታ ላይ አደጋ ገጥሟት ሰጠመች።

የደራሲውን ትንበያ ተአምር የሚያሰኙ በርካታ ተማስሎዎች ነበሩ። የሁለቱም መርከቦች ጉዞ በኢንግላንድና በኒው ዮርክ መሀል የተደረጉ ሲሆኑ፦ የመንገደኞቹ ብዛት፤ የመርከቦቹ ርዝመትና ክብደት እንዲሁም የጫናቸው የነፍስ አድን ጀልባዎች ቁጥር ሳይቀር ተመሳሳይ መሆኑ ራሱ ይገርማል። ሌላው ቀርቶ ታይታን ኤፕሪል 14 ቀን ስትሰምጥ፤ ታይታኒክ ደግሞ ኤፕሪል 15 ቀን ነበር የሰጠመችው።

ይህ እንግዲህ "እንደ ነቢይ" የሚያስደንቁ ካልኳቸው ደራሲያን ተርታ የሚመደብ መሆኑ ነው። በሁለተኛው ረድፍ ወደፈረጅኳቸው ሰፊ ምናብ የታደሉ ደራሲያን ተርታ ስንመጣ ደግሞ ጆርጅ ኦርዌልና "አኒማል ፋርም" የሚለው ስራው ከሚታሰቡን መኻል የሚገኙ ይሆናሉ።

አኒማል ፋርም ከዛሬ 60 አመት በፊት በስታሊን ሩሲያ ውስጥ በተስተዋለ እውነት ዙሪያ እያጠነጠነ የተፃፈ ስለመሆኑ በመፅሀፉ ላይ ምርምር ያደረጉ ሁሉ ይስማሙበታል። ይሁንና ሰፊ ምናብና ብርቱ ብእር ተዋህደው ስለፃፉት እውነቱ ጊዜና ስፍራን ገስሶ፣ ዛሬም በበርካታ አገራት ውስጥ እየተተገበረ ያለ መሆኑ ደራሲውን ታላቅ፣ መፅሀፉንም የሁሉም ዘመን ድርሰት ያሰኙታል።

የእንስሳት አብዮት እኤአ በ1930ዎቹ መጀመሪያ ላይ በአለም የተከሰተውን የታሪክ ሂደት ነበር መነሻው ያደረገው። በአሜሪካ በ1929 ዓ/ም የደረሰው የኢኮኖሚ ቀውስ አለምን ባመሰበት ወቅት በሩሲያ የተወለደውን አብዮት ምርኩዝ አድርጎ- አብዮታዊ ጉዞ እንዴት የአንባገነኖች መፈልፈያ ሊሆን እንደቻለ ያሳየናል። የዛር 'ኒኮላስ ዳግማዊ' - አወዳደቅና የስታሊን አነሳስ የተከሰተው፣ የኢኮኖሚ ድቀትና የነፃነት ድርቅ በቀሰቀሰው ህዝባዊ ቁጣ ነበር። ለህዝቡ ግን እፎይታን ሳይሆን ይብሱኑ ሰቆቃ ማትረፉን "የእንስሳት አብዮት" ጥሩ አድርጎ ፈትሾታል።

ጆርጅ ኦርዌል በካፒታሊዝም ደስተኛ አልነበረም። ይሁንና ሶሻሊዝም የህልም አለም ስለመሆኑም ያመነ ይመስላል። አብዮተኞች እንዴት ለአንባገነንነት ቅርብ እንደሆኑ በወጉ ታዝቧል። የትናንቷን ሩሲያ ብቻ ሳይሆን የዛሬዋንም ኢትዮጵያን የሚፈትሻት ነው የሚመስለው።

ይህንን በየቋንቋው እየተተረጎመና እየተነበበ ዘመናት የዘለቀውን ታላቅ ስራ እነሆ መስፍን ማሞ ይዘቱን በወጉ በሚገልፅ ርእስ "የእንስሳት አብዮት" ብሎ አቅርቦልናል።

የመስፍን ትርጉም ገና በዛሬው እለት ለመመረቅ የበቃ እንደመሆኑ ይህቺ ማስታወሻም ጠቅለል ባለ መልኩ ወፍ በረር እይታ በማድረግ ብቻ ትወሰናለች። በተለይም የትርጉሙን ውበትና በዚህ ዘመን መተርጎሙ ስላለው ፋይዳ ነው መናገር የምፈልገው።

የእንስሳት አብዮትን ሳነብ የትርጉም ስራ መሆኑን እስከ መዘንጋት ደርሻለሁ። ትርክቱ ከአንቀፅ አንቀፅ፣ ከምእራፍ ምእራፍ አንዳች ሳይጎረብጥ ስለሚወርድ ከመሰረቱ በአማርኛ ቋንቋ የተደረሰ ነው የሚመስለው። መልእክቱን ሙሉ ለሙሉ ጠብቆ የአንባቢውን ስሜት እየተቆጣጠረ መዝለቁ የተርጓሚውን የጥንቃቄ ልክና - የብእሩንም ጉልበት ነው የሚያሳየው።

በመፅሀፉ ውስጥ ያሉትን ባህሪያት በወጉ ተስለው ስለምናገኛቸው ከስድስት አስርት አመታት በፊት ሩሲያ ውስጥ ስለነበረው ሁኔታ - በአንድ እንግሊዛዊ ደራሲ እየተደረሰን አይመስለንም። በቅርፅም በይዘትም - ስለ እኛው ዘመን ታሪክ በእኛው አገር ደራሲ እየተተረከልን እንጂ። ለዚህ ስራው ተርጓሚውን በአክብሮት ባርኔጣዬን ከፍ ላደርግለት እወዳለሁ።

በሌላ በኩል ደግሞ ይህን ሃያል መፅሀፍ በዚህ ዘመን ላይ በመተርጎሙ - መስፍን ተገቢ ወቅት ላይ ተገኝቷል ባይ ነኝ። ምክንያቱም "የእንስሳት አብዮት" ኢትዮጵያ ዛሬ የምትገኝበትን ህይወት በአንክሮ እንድንፈትሽም ይረዳናልና ነው።

ቦክሰርና ክሎቨር- ለጉልበታቸው የማይሳሱ ግን ስለመብታቸው የማይጠይቁ በሺህዎች የሚቆጠሩ የዋህ አማኝ ያገሬን ሰራተኞች ያስታውሱኛል። እነኚህ ቅን ዜጎች የአገዛዙን አስከፊነት ብቻ ሳይሆን ፤ የራሳቸውንም ተላላነት ልክ - በመስተዋት እንዲያዩ የእንስሳት አብዮት ይረዳቸዋል። የቦክሰር ፍፃሜ በዘመነ ወያኔም የእያንዳንዱ ታማኝ አገልጋይ ፍፃሜ ነውና። ይህም ከእንቅልፋቸው ያባንናቸው ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

አስተዋይዋ ሙሬል - የተማረውንና የህወሃት/ኢህአዴግን የጥፋት ጎዳና የተረዳውን ወገኔን ነው የምታሳስበኝ። "ያለውን ችግር አወግዛለሁ፤ ግን ቀሪውን ዜጋ ለማስተባበር በቂ ስራ አልሰራሁም። - ይቀረኛል" የሚል ሀሳብ ሊያጭርበት - በዚህም ሊያተጋው ይችል ይሆናል፤ ይህ መፅሀፍ።

ሙሴም ልዩ ባህሪ ነው። በተለይም በየጎዳናው እየዞሩ "የሚደርስብህ በደል ሁሉ እግዜር ስለፈቀደው የሚፈፀም ነውና አሜን ብለህ ተቀበለው" በማለት የሚሰብኩ አንዳንድ አዘናጊ አማኝ ነን ባዮችን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ይመስለኛል።

ክርስቶስ በምድር ቆይታው ለተበደሉ መቆርቆሩን፤ ለተገለሉ መከራከሩንና ስለ እኩልነት መቆሙን ምሳሌ አድርገው ከማስተማር ይልቅ ደንዝዘው የሚያደነዝዙ አንዳንድ ሰባኪዎችን የሞራል ብቃት እንድንጠይቅ የእንስሳት አብዮቱ ሙሴ ያነቃናል።

ለአቶ መለስ መንበር እስከ አሁን ረግቶ መቆየት አይነታ ሚና ያለውን የደህንነት መዋቅራቸውንና ገዳይ ታጣቂዎቻቸውን - በእንስሳት አብዮቱ 'ውሾች' ተማስሎ ማየት እንችላለን። በአእምሯቸው የማይጠቀሙ፤ ህሊና ቢስ አገልጋዮች ሆነው ቀርበዋል። የህወሃት/ኢህአዴግ አባላትና ፓርላማ ውስጥ የሚያንቀላፉ 'ተወከልን ባዮች'፤ እንዲሁም በ አገዛዙ ተጠቃሚ የሆኑ የተወሰኑ ሆድ አደሮች ደግሞ በአሳሞቹ ይወከላሉ። ከእነዚህ መኻል ስንቶቹን ይህ መፅሀፍ ቆም ብለው ማሰብ እንዲጀምሩ ሊረዳቸው እንደሚችል ግን መገመቱ ያዳግታል።

ስኳለር የተባለውን "ጥቁሩን ወደ ነጭ የሚቀይር" ፕሮፓጋንዲስት ስናይ - በርካታ የዘመኑ ፖለቲከኞችና ጋዜጠኞች ይመጡብናል። የኢትዮጵያ ሬዲዮ ከእነዚህ አንዱ ነው። ከፕሬስ እነ ተስፋዬ ገ/አብ ጥለው ወጥተዋል። ዛሬም ሳይለወጡ የሚሰብኩትን ግን ስኳለርን አይተው ራሳቸውን እንዲታዘቡ "የእንስሳት አብዮት"ን እንጋብዛቸዋለን።

በእንስሳት አብዮት ውስጥ ያሉት ባህሪያት በሙሉ በወጉ የተሳሉ ናቸው። መስፍን ደግሞ በውብ አማርኛ ስላቀረበልን በአበሻ መነፅር እንድናያቸው ረድቶናል። መፅሀፉ ደርግንና አገዛዙን ያስታውሰኛል። ያለንበትን የወያኔን ዘመን ደግሞ ቁልጭ አድርጎ ያሳየኛል።

ጆርጅ ኦርዌል ናፖሊዮን የተባለውን መሪ ባህሪ ሲቀርፅ፤ "መለስ ዜናዊ የሚባል አንባገነን ይነሳል" በሚል ትንቢት አልነበረም። ይሁንና የአሁኑ የኢትዮጵያ መሪ ከኦርዌሉ ናፖሊዮን ጋር እጅግ የተማሰለ ባህሪ ይዞ ስናይ በርግጥ ይህ መፅሀፍ ስለዛሬይቱ ኢትዮጵያ የተፃፈ ያህል ነው የሚሰማን።

ናፖሊዮንና ስኖውቦል ራሳቸውን በነፃ አውጪ ስም ለንግስና ያጩ የስልጣን ጥመኞች ነበሩ። ስኖውቦል በመጠኑ ሻል ያለ አእምሮና ህልም ሲኖረው ናፖሊዮን ደግሞ አእምሮው ለሴራ የተሳለና ተቀናቃኙን ውሎ አድሮ ለመጣል ቀድሞ የሚዘጋጅ ፈጣን ጉልበታም ነው። የነዚህ ተቀናቃኞች ፍልሚያና ውጤቱን ስናነብ አቶ መለስ በትግሉም ወቅት ሆነ

ከቤተ መንግስት ሆነው የስልጣን ተጫራች ተጋዳላይ ጓዶቻቸውን እንዴት ጠልፈው እንደጣሏቸው ነው የሚታሰበን። (አቶ አረጋዊን በበረሃ፤ አቶ ስዬን በአዲስ አበባ ያስታውሷል)

ናፖሊዮን አጀማመሩ እንደ አንድ ሩቅ አላሚ ታጋይ ነበር። መሪ ሆኖ ገመናው ሲገለጥ ግን አንባገነንነቱ ገጦ ይወጣል። ሌላው ቀርቶ የእንስሳቱ አብዮት አልሞ የተነሳበትን ፕሮግራም ሳይቀር በየፌሮማታው ላይ ሸርሽሮ ሲጥለው እናስተውላለን። የመብትና የ እኩልነት መርሆች በአስደናቂ ፍጥነት እየተቀነጣጠሱ ይወድቃሉ። እናም መሪው ስልጣኑን ሁሉ ጠቅልሎ በቅንጦትና በተድላ ሲኖር እናገኘዋለን። ያሻውን ገድሎ፤ ላሻው ሰጥቶ።

ይህ ድርጊት በተለያዩ አገራት ካሉ አንባገነኖች ጋር ይስማማ ይሆናል። የአቶ መለስን ያህል ግን ልክክ ብሎ የሚገጥምለት ሰው ያለ አይመስለኝም። ሰውዬው በረሃ እያሉ ስለ ብሄር ብሄረሰቦች መብት መከበር ይሰብኩ ነበር። እንሆ በተግባር ደግሞ በብሄር እየለኩ የሚያገልሉ እና የሚደቁሱ ሆነው ተገኙ። ስለ አብዮተኝነታቸውም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ነበር የሚሰብኩት። ያውም የአልባኒያውን ኢንቨር ሆዣን እያወደሱ። ዛሬ ደግሞ ነፃ ገበያን ተቀብያለሁ ይላሉ። የገበያው ነፃነት ግን ለቤተሰቦቻቸውና በዙሪያቸው ለሚያጫፍሩ ጥቂቶች ብቻ ሆኖ ተገኘ። አንዳንዶች ይበልጥ እኩል ናቸውና።

የእንስሳት አብዮት በርግጥ ዘመን ያልሻረው፤ ዛሬም ህያው የሆነ መፅሀፍ ነው። ይህ ወቅት ደግሞ ከመቼውም ጊዜ በላይ ሊነበብ የሚገባው ግዜ ይመስለኛል። በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ እየተስተዋለ ያለው ህዝባዊ እንቅስቃሴ ላገሬ ብዙ የሚያስተምራት ሀቅ አለ። አይደረሴ መስለው የሚኮፈሱ አንባገነኖች፤ የተቀናጀ የህዝብ ቁጣ ከተነሳባቸው በሳምንት የሚናዱ የእንቧይ ካቦች መሆናቸውን ከሙባረክና ከቤን አሊ በላይ ምስክር የለም። እነሆ የእንስሳት አብዮት ደግሞ የበኩሏን አስተዋፅኦ ልታደርግ ቀርባለችና - አጣጥሚት። …

በመጨረሻም ይህችን ማስታወሻ ከማጠቃለሌ በፊት "የእንስሳት አብዮት"፦ እንስሳትን ተምሳሌ አድርጎ ማቅረቡ የሚያስታውሰኝን አንድ የአገሬን ታሪክ ላንሳ።

ጆርጅ ኦርዌል በተወለደበት ዘመን ነበር በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ተውኔት ለእይታ የበቃው። ደራሲው በጅሮንድ ተ/ሃዋርያት ተ/ማርያም ይባላሉ። በወቅቱ ፈረንሳይ ውስጥ ቆይታ አድርገው ስለተውኔትም እውቀት ገብይተው ነበር የተመለሱት። ይሁንና ከፓሪስ መልስ ቲያትር እየተባሉ አገር ቤት የሚቀርቡት ስራዎች የአዝማሪ ጨዋታዎች ብቻ በመሆናቸው ያዝኑና ብእራቸውን ያነሳሉ።

ይህ በበጅሮንድ የተደረሰው የመጀመሪያው ተውኔት በ1911 ዓ/ም ለእይታ በቅቶ ጉድ አሰኘ። ልክ እንደ ጆርጅ ኦርዌል "አኒማል ፋርም" ሁሉ የበጅሮንድም ተውኔት እንስሳትን ተምሳሌ አድርጎ ነበር የቀረበው። ርእሱም "የአራዊቶች ኮመዲ" ይሰኛል። ሌላው አስገራሚ ተማስሎ ደግሞ የአውሬዎች ኮመዲ እንደ እንስሳት አብዮት ሁሉ ምፀታዊ ስራ መሆኑ ነው።

ተውኔቱ የልጅ እያሱን ያልበሰሉ የህፃን ድርጊቶች ይተቻል። በንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ ምኒሊክና በሃይለ ስላሴ መኻል ያለውን የስልጣን ሽኩቻም ያጋልጣል። በወቅቱ በተንሰራፋው ንቅዘትና የስልጣን ብልግና ላይም ይሳለቃል። በተውኔቱ ላይ ዝነኛ ጉቦኛ ሆና የቀረበችው ጦጣ የአራዊቱ ንጉስ በሆነው በአንበሳ ዳኛ ሆና ስትሾም በማሳየት የ አገሪቷ ችግር መነሻው ከአናቱ መሆኑን ያመለክታል።

ተውኔቱ በንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ ትእዛዝ ወዲያውኑ ታገደ። በዚህም ዛሬም ድረስ በኢትዮጵያ ነግሶ ያለው የብእር አፈና የመጀመሪያው ሰለባ ለመሆን በቃ።

*መልካም ንባብ እመኝላችኋለሁ!*

*ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ!*

***<u>ማስታወሻ</u>***

***ይህ ፅሁፍ ኤፕሪል 17 2011 የእንስሳት አብዮት መፅሀፍ ሲድኒ አውስትራሊያ ውስጥ በርካታ ኢትዮጵያዊያን በተገኙበት የምረቃ ስነ ስርአት ላይ የቀረበ ነው።***

**የእንስሳት አብዮት *መፅሀፍን ማግኘት ለምትፈልጉ እነሆ የተርጓሚው ኢሜል አድራሻ፡-***

msfntessema@yahoo.com.au